# ከወንጀለኛ ጋር መደመር የወንጀለኛ ተባባሪ መሆን ነው

(ከአይናዲስ ተሰማ)

August 26, 2018

ሕግ ወንጀለኞችን ለመቅጣት/ለማረም ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ሰው ወደወንጀል እንዳይገባ ለመከላከል ማስተማሪያ/ማስፈራሪያ ሆኖ የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ወንጀለኛ ሰው ለህግ ቀርቦ ሲቀጣ የሚያይ ሌላ ግለሰብ ጉልበቱን፣ ስልጣኑን ወይም ሀብቱን ተማምኖ ወንጀል ሊፈጽም አይነሳሳም። ህግ የተላለፉ ሰዎች በፈጸሙት ጥፋት ተጠያቂ ሲሆኑ፣ ወንጀል የተፈጸመባቸው ወገኖችም በህግ ፍትህን እንዲያገኙ ሲደረግ ሁሉም ህግን አክብሮና ተማምኖ ወደመኖሩ ይገባል። ለዚያም ነው ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች/ድርጅቶች በህግ መጠየቅ አለባቸው የሚባለው።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የጦር ወንጀል የፈጸሙ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎች ለብዙ አስርት አመታት ከየተደበቁበት እየታደኑ ለህግ ቀርበዋል። በደርግ ጊዜ የቀይ ሽብር ወንጀል ፈጽመዋል የተባሉ ሰዎችም ብዙወቹ ለረጅም አመት በሀገር ቤት በእስር ተቀጥተዋል። በውጭሀገርም ለምሳሌ በሆላንድ ተይዘው የታሰሩ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ናቸው የተባሉ ሰው አሉ። ይህ ጉዳይ በኢሕአዴግ ጊዜ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችንም/ቡድኖችንም የሚመለከት መሆን አለበት። እንዲያ ካልሆነ ፍትህ የለም ማለት ነው። ፍትህ-አልባ ይቅርታ ደግሞ ቀልድ ነው።

ፍትህን መጠየቅ ማክረር ወይም ጽንፈኛ መሆን አሊያም ለበቀል መነሳሳት ማለት አይደለም። ፍትህን መጠየቅ ህጋዊነትን ማረጋገጥ እንጅ በቀለኛ መሆን ማለት አይደለም። ፍትህ በቀል አይደለም። በቀል ማለት ከህግ አግባብ ውጪ በራስ ተነሳሽነት የሚፈጸም የአጸፋ መልስ ነው። እኛ እያልን ያለነው ወንጀለኞች ለህግ ይቅረቡ፤ ፍትህ ይሰጥ ነው።

ወንጀል በየትኛውም ግለሰብም ይሁን ማህበረሰብ ዘንድ የሚወገዝ አፍራሽ ተግባር ነው። ወንጀል የሚፈጸመው በህገወጥ ሰዎች መሆኑ ይታወቃል። ህግ የማይገዛቸው ህገወጦች የትም አሉ፤ ወንጀለኛ ዘር የለውም። ወንጀለኞች ዘርን የሚጠቀሙት ለምሽግነት ብቻ ነው። ማናችንም ብንሆን ለህገወጦች ከለላ መስጠትና ተከራካሪ ሆነን መቆም አይኖርብንም። ወንጀለኛን መደበቅ ወይም በተለያየ መንገድ መደገፍ ህግን ተጻርሮ መቆም ነው።

የግለሰብና የሀገር ሀብት የዘረፉ ሰዎችም ሆኑ ድርጅቶች የወሰዱትን ነገር በሙሉ ለባለቤቱ መመለስ ይኖርባቸዋል። ካለህግ አግባብ የተገደሉ፣ የተፈናቀሉ፣ የተዘረፉ፣ የተገረፉ፣ የታሰሩ፣ — ሰዎች በተለይ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በጥቅል፣ ይቅርታ ሊጠየቁና ሊካሱ ይገባል። ይህን ለማድረግ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም የደረሰውን ሰብአዊና ቁሳዊ ጥፋት በተመለከተ ጥልቅ ጥናት ማካሄድና ወንጀለኞችን የመለየት ስራ መስራት ያስፈልጋል። የተፈጸመውን ወንጀል የማጥናት፣ ወንጀል ፈጻሚወችን የመለየት፣ ሥራ በገዥው መንግስት ያንድ ወገን ጥረት ብቻ የሚፈጸም አይሆንም። ዕውነተኛ ለውጥ እያደረግን ነው ካልን ለውጡን የሚመራ የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ የስራ ክፍፍል ማድረግ ተገቢ ነው። እንዲያ ሲሆን ለሁሉም የባለቤትነት ስሜት ስለሚፈጥር ተሳትፎን በማሳደግ ሥራን ያቃልላል፤ አመኔታንም ይፈጥራል።

በመሰረቱ አውቀን በድፍረት ሳናውቅም በስህተት ለፈጸምነው በደል ይቅር የምንባባለው ሕዝብ ለሕዝብ እንጅ ከወንጀለኛ ጋር በፍጹም ሊሆን አይችልም። ወንጀለኛ ይቅርታን የሚያገኘው ለፍትህ ሲቀርብ ነው። ያም ሆኖ ይቅርታ የማያሰጡ ወንጀሎች መኖራቸውን ማሰብም ተገቢ ነው። ምንም ሆነ ምን ከየትኛውም ወገን ያሉ ጥፋተኞች ወደህግ ቀርበው ጉዳያቸው በፍርድቤት ሊታይና ፍትህ ሊሰጥ ይገባል። ከዚያ ውጭ ዝም ብለን ይቅር እንባባል ማለት ወንጀለኞችን በገደላችሁት አትጠየቁም፣ የዘረፋችሁትን ገንዘብም የሚነካባችሁ የለም ብሎ ለወንጀለኞች ሽፋን መስጠት ብሎም ወንጀልን ማበረታት ይሆናል። እንዲህ አይነት አመለካከት ያለው ሰው ካለ ያ ሰው ወይ ከወንጀለኞቹ አንዱ ነው አሊያም የወንጀለኞች ቅጥር ነው። ሰው/ሕዝብ ገድሎና ለመከራ ዳርጎ፣ ስልጣንን መከታ አድርጎ ወይም ከባለስልጣን ጋር ተሞዳሙዶ የግልና የሀገር ሀብት ለግል ጥቅሙ አውሎ እያለ የወሰደውን ሳይመልስ በገደለውም ሳይጠየቅ ያለፈውን ረስተን ዝም ብለን ይቅርታ ብቻ እናውረድ የሚባል ከሆነ አቅሙ ኖሮን እኛም ተመሳሳዩን አድርገን ቁስላችን ከሻረ፣ የተነጠቅነውንም ካስመለስን በኋላ ያኔ ይቅርታውን እናድርገው የሚል የበቀል ስሜት ይፈጥራል። ሕግ ሊፈታው ያልቻለውን ችግር ተበዳዮች በራሳቸው መንገድ ፍትህ ነው የሚሉትን ነገር እንዲያደርጉ ማለትም ለበቀል እንዲነሳሱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የተረጋጋ ሀገርና ህግ አክባሪ ሕዝብ እንዲኖር ከተፈለገ ፍትህ መስፈን ይኖርበታል።

በይቅርታ የመደመር የውይይት መድረክ ላይ ከቤንሻንጉል የመጡ ሰው የብሔር ጭቆና እንደነበረ ሲናገሩ ሰማሁ። ይህ ወያኔና ሌሎች በአማራው ላይ ጥላቻ ያላቸው ሰዎች ደጋግመው የሚያነሱት ጉዳይ ነው። እኒህ ወገኖች አማራውን ጨቋኝ ብሔር ሌሎቹን

ደግሞ ተጨቋኝ አድርጎ የመመልከት በሽታ ሲያሰቃያቸው ኖሯል። ይህ ግን ፍጹም ስህተት ነው። በመሰረቱ በነገስታቱ ጊዜ ኢትዮጵያ ትተዳደር የነበረችው ከእስራኤላዊው ንጉስ ሶሎሞን ተወላጆች በሆኑት ሰዎች ነው። ንግስት ሳባ እስራኤል ሄዳ ቀዳማዊ ሚኒሊክን ጸንሳ ከተመለሰች በኋላ ሶሎሞን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘው የንጉስ ዳዊት ልጅ በመሆኑ ፈጣሪ ለንግሥና የፈቀደው ለእርሱ ዘር ነው በሚል "ሞአ አምበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" እየተባሉ ነው ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ የነበሩት። እኒህ ነገስታቶች የሕዝብ አንድነት ለመፍጠር በሚል እሳቤ ከአማራ፣ ከትግሬ፣ ከኦሮሞ፣ ከህዲያ፣—ባላባቶች ጋር እየተጋቡ የተዋለዱ ናቸው። በዚህም መሰረት በንጉስነት ያስተዳድሩ የነበሩ ሰዎች የሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ደም ያለባቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በጉልበታቸው ወደስልጣን የመጡ ከሶሎሞን የዘር ሀረግ የማይመዘዙ አማራነት የሌለባቸውም እንደነበሩ ይታወቃል። ለምሳሌ ዮዲት ጉዲት ፈላሻ ነበረች፣ የዛጉዌ ስርዎመንግስት ነገሥታት በሙሉ አገዎች ነበሩ፤ አጼ ቴወድሮስ ቅማንት ናቸው ሲባሉ እየሰማን ነው፡ ግራኝ አህመድ አዳል/ኢሳ ናቸው፣ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያምም ኦሮሞ። ይሁን እንጅ ወያኔ፣ ኦነግም ይሁን ሌሎች ተገንጣይና አፍራሽ ሀይሎች በዙሪያቸው ደጋፊወችን ለማሰባሰብ እንዲያስችላቸው አንድ የጋራ ጠላት መፍጠር ነበረባቸው። በዚህም ምክንያት በተለይ ከምንም በላይ ሀገሩን የሚወደውን አማራ ገዥና ጨቋኝ ብሔር እንደሆነ አድርጎ ታሪክ በመፍጠር ደጋፊ ለማሰባሰብ ተቻለ። አማራው ጨቋኝ ብሔር ነበር እንዲባል ያበቃው ሀገሩን መውደዱና መከላከሉ ሳይሆን ይቀራል! በሕዝብና በሀገር አንድነት ጠበቃነቷ የተነሳ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም ከአማራ ጋር ተደምራ የጥቃት ሰለባ ሆና ቆይታለች። ሌላው የቤንሻንጉሉ ሰው ያነሱት ነጥብ አንቀጽ 39 የብሄረሰቦች አብሮ የመኖር ዋስትና ነው የሚለውን ቀልድ ነው። የኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል ፕሬዚደንት የነበሩት ሰው ከተከሰሱባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ክልሉን ለመገንጠል እየሰሩ እንደነበረ ስለተደረሰባቸው ነው የሚል ነው። የመገንጠል መብትን በህገመንግስት አካቶ ነገር ግን ይህን ህገመንግስታዊ መብት ለማከበር የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች ማሰር ቀልድ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል! ሊተገበር የማይችል መብት ከሆነስ ለምንድን ነው በህገመንግስት ውስጥ እንዲካተት የተደረገው? የጉድ ሀገር! ማለት ይኼኔ ነው።

ሀገር በልዩነት ይመራል የሚል ዕምነት የለኝም። ይህ ማለት ግን ሁላችንም በሁሉም እረገድ አንድ መሆን አለብን እያልሁ አይደለም። እያልሁ ያለሁት የሀገር ሉአላዊነትና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጉዳይ የጋራ አጀንዳችን ይሁኑ ነው። ለዚህም ያመች ዘንድ የአንድነቱን ጎራ ለማጠናከር የሚደረገው ትግል መቀጠል እንዳለበት እኔም አምናለሁ። ይህ የሚሆነው ግን የአማራ ድርጅቶችን በማዳከም አይደለም። ይኸው ዛሬም አማራው ጨቋኝ ነበር እየተባለ በጠላትነት ከመታየት አልወጣም። እንዲህ ያለ የጥላቻ መንፈስ ባለበት ወቅት ተዳክሞ መገኘት ጥሩ ውጤት አያመጣም። ባልተደራጀንበት ጊዜ የሆነውን እናውቃለን። ዛሬም ቢሆን ምን እየተካሄደ እንደሆነ እንገነዘባለን። ሌሎች የጎሳ ድርጅቶች እየተጠናከሩ እንጅ እየከሰሙ አይደለም። በዚህ ሁኔታ አማራውን በዘርህ አትደራጅ ማለት ከጠላትነት ተለይቶ የሚታይ አይሆንም። የምትደራጁ ከሆነ በየቦታው የተበተኑት ወገኖቻችሁን ለአደጋ እንደምታጋልጡ እወቁ ብለው የሚያስፈራሩን ሰዎች እየተደመጡ ነው። ሌላው ይደራጅ፤ እናንተ ግን ተበታትናችሁ የሚደርስባችሁን ሁሉ በጸጋ መቀበል ነው ያለባችሁ ማለት ወዳጅነት ሊሆን አይችልም።

የአማራ ድርጅቶች ልዩነቶችን ወደጎን በማድረግ በአንድነት መቆም ይኖርባቸኋል። ብአዴንን ማክበርና ማቅረብ ተገቢ ነው። በአማራው ክልል የበላይነቱን የያዘው እርሱ ሆኖ እያለ እየወሰደ ያለው የለውጥ ተግባር የሚያስመሰግነው ነው። ድርጅቱ አቅም ባልነበረው ጊዜ ውስጥውስጡን እንደኛ ሲታመሙ የኖሩና ለውጥ ለማምጣት እንቅልፍ አጥተው ሲሰሩ የነበሩትን የድርጅቱን አባላት ወንድም እህቶቻችንን ልናቅፋቸው ይገባል። በአማራ ክልል ተቃዋሚና ገዥ የሚባል አማራም ሆነ ድርጅት በአሁኑ ወቅት የሚታሰብ መሆን የለበትም። አማሮች ያልተመለሱ ብዙ ጥያቄወች አሉን። ዛሬም በባርነት ተይዘው እየጮሁ ያሉ ወገኖቻችን አሉ። ባልተወከልንበት ወቅት በጸደቀው ህገመንግሥት፣ ህገመንግስቱን መሰረት አድርገው በተፈጸሙ ድርጊቶች ያጣናቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ገዳይና አስገዳዮቻችን ለህግ አልቀረቡም። ዛሬም ቢሆን በዚያው በተለመደው መንገድ በጠላትነት የሚያዩን፣ ውድቀታችንን የሚመኙ፣ ብዙ አሉ። ጠላት ነው ተብሎ የተፈረጀው አማራ ብቻ ነበር፤ በመርሀግብር ደረጃ ጠላት ስለሆነ መጥፋት አለበት የተባለ ከአማራ ውጪ ማንም የለም፤ ዛሬም ከዚያ የተለየ አረዳድ የለም። ይህንን ሁኔታ መቀየር የምንችለው በትግል ነው። ከኦህዴድና ከመሰል የለውጡ ኃይሎች ጋር በመተባበር ኢትዮጵያዊነትን ማጽናትና ዘላቂ ሰላም ማምጣት አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ግን ወንጀለኛን በመሸለም መሆን የለበትም።

ኤርትራ ስህተቷን እያረመች ይመስላል። ኢትዮጵያን ሰላም እንዲነሱ እያሰለጠነች የምትልካቸውን ተገንጣይ ኃይሎች ፊት እየነሳች እንደሆነ ነው እየሰማን ያለነው። በዚህም ምክንያት ብዙወቹ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወደኢትዮጵያ እየገቡ ነው። የትህዴን ጉዳይ ምን እንደታሰበለት አይታወቅም። ኤርትራ በወያኔ ተንኮል መቸም የማይረሳ በደል ደርሶባታል። የተባበሩት መንግስታት በጣለባት ማዕቀብ መራራ ጊዜ ውስጥ ናት። ከወያኔ ጋር በነፍስ የሚፈላለጉ ባላንጣወች ሆነዋል። ለኢኮኖሚው ዕቀባ የወያኔ ግፊት አለበት። የ 1990 ው የሁለቱ ሀገሮች ጦርነት ምክንያት ነው ተብሎ የተገለጸው እና አሁንም እየተባለ ያለው ለማንም የማይዋጥ ተራ ሹፈት ብዙ ጎድቷታል። ለሁለቱ ሀገሮች ወደጦርነት መግባት በምክንያትነት የተጠቀሰው ነገር ኤርትራ ኢትዮጵያን በመውረሯ ነው የሚል ነው። በወረራ ያዘችው የተባለው ቦታ ደግሞ ባድሜ ነበር። ከጦርነቱ በኋላ ባድሜ የኤርትራ ነው ተብሎ ተፈርዷል። ይህም ማለት ቀድሞውኑ ባድሜ በኢትዮጵያ ስር ከነበር ኢትዮጵያ ያላግባብ የሌላ ሀገር መሬት ይዛ ነበር ማለት ነው። የኤርትራ

ጦር ባድመ ሲገባ ኢትዮጵያን ወረረ ሊባል አይችልም። ሊባል የሚችለው ግዛቱን አስከበረ ወይም ያላግባብ በኢትዮጵያ ተይዞበት የነበረውን መሬት አስመለሰ ነው። በጦርነቱ ወቅት በባሬንቱ በኩል ተሰልፎ ይዋጋ የነበረ ኤርትራዊ ጋር ስናወራ በኢትዮጵያ ጦር ከደረሰባቸው ጥቃት ይበልጥ የትግራይ ህዝብ የፈጸመባቸው ግፍ እንደሚያመው ነው የተረዳሁት። "የወያኔን ሰራዊት ስናሰለጥን ግራና ቀኝ እጆቻቸውን መለየት የማይችሉ ስለነበሩ ከፊት የእኛን ሰው አቁመን ከኋላው ያለው የወያኔ ወታደር ጋር የቀኝ እጆቻቸውን በአንድ ላይ እንዲሁም የግራ እጆቻቸውን በአንድ ላይ በገመድ አያይዘን ስናበቃ ግራ ስንል የግራውን፣ ቀኝ ስንል ደግሞ የቀኝ እጁን ወደፊት እየጎተተ እንዲመልስ በማድረግ ነበር ግራና ቀኝ እጆቻቸውን እንዲለዩ ያሰለጠንናቸው። ያለንን እያካፈልን እና እያሰለጠንን ለስልጣን ያበቃናቸው ወያኔወች የሚጣሉት ቢያጡ እኛን ጠላት ብለው በህሰት ክስ ወጉን። የትግራይ ሕዝብ ደግሞ ከጦሩ ኋላ ኋላ እየተከተለ በየቤቱ እየገባ ማንከሽከሻ ሳይቀር ሙልጭ አድርጎ ዘረፈን" አለኝ። ከኤርትራ ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ሽፍጥ በሌለው፣ ነገር ግን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በሚያስማሙ ነገሮች ላይ አብሮ መስራት ይቻላል።

ዋናው ነገር ግን የአማራ ኃይሎች በአንድነት መወያየትና የጋራ አጀንዳ ላይ ማተኮር ከአሁኑ መጀመር አለበት።

ትንሳኤ ለአማራ!

ትንሳኤ ለኢትዮጵያ!